# ጽንፈኝነት እና በኢትዮጵያ ሁኔታ የሚገለጽበት አግባብ

**ሰለሞን ሽፈራው** 11-04-17

ከሰሞኑ "ጽንፈኝነትና ዓለም አቀፋዊ ገጽታው" በሚል ርዕስ ያቀረብኩትን ፅሑፍ ሳጠቃልል ቃል በገባሁት መሰረት ጉዳዩን ከኛ አገር ሁኔታዎች አኳያ አንስተን የምንመለከትበትን አግባብ ለመጠቆም ያለመ ሃሳብ ይዤ መጥቻለሁ። ሰለዚህም ለሽብርተኝነት ተግባር መበራከት ሁነኛ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደው አንድን የሃይማኖት፤ ወይም ደግሞ የፖለቲካ እሳቤ ለቡድናዊ ፍላጎት ማስፈፀሚያነት እንዲያመች አድርጎ በማክረር የማቀንቀን አባዜ፤ ለምን ፅንፈኝነት ነው ሊባል እንደሚችል ለማብራራት በመሞከር ብጀምር መልካም መስሎ ይሰማኛል። ምክንያቱም ደግሞ፤ በተለይም እዚህ እኛ አገር ውስጥ "ጽንፈኝነትም፤ ሽብርተኝነትም ለኢትዮጵያ አሳሳቢ ችግር ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም" እያሉ ጉዳዩን ገዢው የፖለቲካ ፓርቲ ሆነ ብሎ ስልጣኑን ለማስጠበቅ ሲል የፈጠረው ማስፈራሪያ እንደሆነ ለማስመሰል ሲሞክሩ የሚስተዋሉ ተቃዋሚዎች እንዳሉ ይታወቃልና ነው።

ከዚህ አኳያ የተሻለ አስረጂ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል የምለው መሰረታዊ ነጥብ ደግሞ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በመላው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍና ተቀባይነትን ያተረፈችበትን፤ የፀረ ሽብር ሕግ ጨምሮ፤ የሲቪክ ማህበራትንና መንግስታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲባል የወጡ አዋጆችን ሁሉ ተቃዋሚዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ምን ያህል አምርረውና አክርረው ሲያብጠለጥሏቸው (ሲያወግዟቸው) እንደሚደመጡ ማስታወሱ በቂ ነው። ከዚህ የተነሳም፤ የኢፌዲሪ መንግስት የሚከተለውን የፀረ ሽብርተኝነት ትግል ስትራቴጂ በተመለከተ አድናቆቱን የማይገልፅ ዓለም አቀፋዊ ባለድርሻ አካል ያለመኖሩን ያህል፤ አብዛኛው የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ይሄን ጠንካራ ጎናችንን ከነምክንያቱ አብጠርጥሮ በማስቀመጥ ረገድ ድፍረት እንደሚያንሰው ደፍሮ መናገር ይቻላል።

እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ፤ እቺ ሀገር የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና፤ የዘመኑ ዓለም አሳሳቢ የጋራ ደህንነት ስጋት ከሆነ የሰነባበተው፤ የፅንፈኛ ቡድኖች አፍራሽ እንቅስቃሴና እንቅስቃሴው የሚገለፅበት ጅምላዊ የሽብር ጥቃት በጎላ መልኩ ተባብሶ ሲቀጥል የሚስተዋልበት ግንባር ቀደም የአደጋው ተጋላጭ አካባቢ ሆኖ ሳለ፤ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ቀልብ እየሳበ ያለውን አስተማማኝ የሰላምና መረጋጋት በጎ ገፅታ ለማስፈን መቻሉ ሊደነቅ የሚገባው፤ የፀረ ሽብርተኝነት ትግላችን ድምር ውጤት የመሆኑን ጥሬ ሀቅ አምነው ላለመቀበል ሱባኤ የገቡ የሚመስሉ ሚዲያዎች ጥቂት አይደሉም። ለዚህ አስተያየቴ መነሻ ምክንያት ከሆኑኝ የሀገር ውስጦቹ የግልና የመንግስት (የህዝብ) መገናኛ ብዙኃን መካከል በተለይም አንዳንዶቹ፤ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ እየተስተዋለ ያለውን የሁከትና ብጥብጥ ተግባር በማራገብ ረገድ የሚያሳዩትን የተጠና ክትትል ላይ የተመሰረተ የሚመስል እንቅስቃሴ ልብ ብሎ ለሚታዘብ ሰው ደግሞ፤ የፀጥታ መደፍረስ ችግሩን መኖር ከሚፈልጉት ፅንፈኛ ተቃዋሚ ቡድኖች ጋር፤ እጅግ የጠበቀ ትስስር አላቸው ብለን እንድናምን የሚያስገድድ ሆኖ ቢሰማን አያስገርምም።

እናም ከዚህ አኳያ እኔ እንደ አንድ የሀገራችንን ወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳት ከመታዘብ ቦዝኖ የማያውቅ ዜጋ፤ የፅንፈኛ አስተሳሰብ መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደውን፤ ደም አፋሳሽ ግጭትና የጎዳና ላይ ነውጠኝነት፤ እንደ አዋጭ የትግል ስልት ለወሰዱት ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ልሳን ሆነው የሚያገለግሉ መስለው የሚስተዋሉበትን አሉታዊ ዘገባ በማቅረብ የተጠመዱትን የመረጃ ምንጮች በሚመለከት፤ ተጨባጭ ማሳያዎችን እያነሳሁ መከራከሪያዬን ምክንያታዊ ማድረግ እችላለሁ። እንግዲያውስ በኢትዮጵያ ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ ውስጥ የፅንፈኝነት ተግባርም ሆነ አስተሳሰብ የሚገለፅበትን አጠቃላይ እንቅስቃሴ፤ በማባባስ ረገድ ቁልፍ የሚባል አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ስለመሆኑ ተደጋግሞ የሚነገርለት ዘመን አመጣሹ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ እየታየ ያለውን ጽንፈኝነት ላስቀድም። የሀገራችን ህዝቦች ለወትሮው ከሚታወቁበት ፈሪሃ እግዚአብሔርን ያማከለ ዕርስ በርስ የመከባበርና የመረዳዳት ጠቃሚ የጋራ ባህል እጅጉን ያፈነገጠ ጋጠወጥነት ጎልቶ በሚንፀባረቅበት ጭፍን የጥላቻ ስሜት፤ የብሔር ተወላጅነትን መሰረት

ያደረገ ጎራ እየለዩ መፈራረጅን እንደፈሊጥ የያዙት ዜጎች ለምን ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየተበራከተ እንደሚመጣ፤ እያንዳንዳችን ራሳችንን እንጠይቅ ዘንድ ግድ የሚል ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ እኔ በግሌ።

ምክንያቱም፤ በማህበራዊ ሚዲያ ገፆች ላይ በለየለት ፀያፍና አስነዋሪ የዘረኝነት ቋንቋ የሚፃፉ ተራ የስድብ መልዕክቶችን እያዛመቱ፤ አንዱን የብሔር ወይም ደግሞ የብሔረሰብ ህዝብ በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ላይ በጥላቻ ለማነሳሳት ያለመ መርዘኛ ሃሳባቸውን ሊያጋቡብን ሲሞክሩ የሚስተዋሉት ግለሰቦች፤ እዚሁ ከኛው መሀል የተገኙ የእያንዳንዳችን ሞራላዊ ድቀትና ስነምግባራዊ ዝቅጠት ድምር ውጤቶች እንጂ፤ ከሌላ ዓለም የመጡ ባዕዳን ፍጡሮች አይደሉምና ነው። ታዲያ ከአብዛኛው የዚች አገር "ተራ" ህብረተሰብ የተሻሉ ተደርገው የሚቆጠሩት ልሂቃን ዜጎቻችን፤ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ መሳፍንታዊ የፖለቲካ ሴራ በሚመነጭ መቧደን መክንያት ጎራ ለይቶ ዕርስ በርስ መጠላለፍንና አብሮ ከማደግ ይልቅ ተያይዞ መውደቅን እንደጠቃሚ ባህል ሲቆጥሩት እየተስተዋሉ ባለበት ሁኔታ ውስጥ፤ ተወልደው ያደጉት ወጣት ልጆቻቸውን፤ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚያሳዩትን ዓይነት የጭፍን ጥላቻ ስሜት ማንፀባረቃቸው ለምን ያስገርመናል ወገኖቼ!? መቼስ ሰው የዘራውን ማጨዱ አይቀርም አይደል? ስለዚህም እንደኔ እንደኔ በወጣቶቻችን አሉታዊ አዝማሚያ ላይ መፍረድ ብቻውን መፍትሔ አይሆንም ባይ ነኝ።

እስቲ ለማንኛውን አሁን አሁን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቀለም ቀመስ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በአስተሳሰባቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የፅንፈኝነት ዝንባሌ ያለውን የትምክህት፤ ወይም ደግሞ የጠባብ ብሔርተኛ አመለካከት መገለጫ ፖለቲካዊ አቋም ያዘለ መልዕክት ይለዋወጡበታል ተብሎ የሚገመተው ማህበራዊ ሚዲያ ጭፍን ጥላቻን እንደወረርሽኝ በማዛመት ረገድ የሚጫወተው ጎጂ ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሌሎች የመገናኛ ብዙኃን ዘርፎችስ ተጠቃሹን ችግር ከማባባስ አንፃር ሲታይ እውን ከወቀሳ የሚያድን ሚዛናዊ ዘገባ በማቅረብ የሚታወቁ ናቸውን? ወደሚል ጥያቄ እንለፍ። ስለዚህም እንደኔ ትዝብት ከሆነ፤ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተባባሰ የመጣውን የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፅንፈኛ አስተሳሰብ ወልዶ በማሳደግ ረገድ፤ ማናችንም ብንሆን "ከደሙ ንፁህ ነኝ" ለማለት የሚያስችል ሞራላዊ ብቃት የለንም የሚል ምላሽ ለመስጠት እገደዳለሁ። ይሄን የምለውም ከሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚመነጭ አሳማኝ መከራከሪያ እንጅ እንዲያው ነገር ማክበድ አምሮኝ እንዳይመስላችሁ።

ስለዚህ ማንኛችንም ከተወቃሽነት ነፃ እንዳንሆን የሚያደርገን የመጀመሪያው መሰረታዊ ምክንያት፤ ጥቂት የየራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ለማሳካት የሚሹ ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ልሂቃን የእነርሱን ጠባብ ፍላጎት ለማስፈፀም ባለመ ቡድናዊ እንቅስቃሴያቸው አማካኝነት፤ አንዱን የብሔር፤ አልያም የብሔረሰብ ህዝብ እንደ ህዝብ፤ በጠላትነት ለመፈረጅ የሚቃጣውን አክራሪ አቋም ሲያራምዱ እያየን፤ ከማውገዝ ይልቅ ከቶውንም "ጎሽ አበጃችሁ፤ በርቱልን!" እንደ ማለት የሚቆጠር ድጋፍ ስንሰጥ የምንስተዋልበት አግባብ መኖሩ ነው። ሁለተኛውና ከዚሁ ነጥብ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚገልጽ መሰረታዊ ምክንያት ደግሞ፤ ወጣት ልጆቻችንን ከጭፍን ተቃውሞና ከጭፍን ድጋፍ በሚመነጭ ተራ ስሜታዊነት እየተገፋፉ (እየተነዱ) ለጽንፈኞቹ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ አቀንቃኝ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች የጥፋት ተልዕኮ ማስፈፀሚያ የመሆን ሙከራ አስከማድረግ የመድረሳቸው ጉዳይ ነው። ተደጋጋሚ የሁከትና ብጥብጥ ሀገር አውዳሚ ተግባር ላይ ተሰማርተው በመገኘት ትርጉም የለሽ የህይወትና የንብረት ኪሳራ ያስከተለብንን የነውጠኝነት እንቅስቃሴ ካሳዩ በኋላ እንኳን፤ ጉዳዩ ከወዲሁ ዘላቂ መፍትሔ ካልተፈለገለት በስተቀር የጋራ ህልውናችንን ለከፋ አደጋ ሊያጋልጥ እንደሚችል የተሰማን ህዝቦች አለመምሰላችን ደግሞ ይበልጥ ያስገርማል።

መንግስት፤ እንዲሁም ደግሞ መላው ህብረተሰባችንና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፤ ወደ አንድ የአስተሳሰብ ፅንፍ ያለቅጥ ጭልጥ ብሎ የሚነጉድ አክራሪ የፖለቲካዊ አቋም መገለጫ አመለካከትን አምርሮ ስለመታገል አስፈላጊነት ጉዳይ፤ ትርጉም ያለው ሀገራዊ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ የሚጠበቅብን ስለመሆኑ መተማመን ለመፍጠር የሚያስችል ግልጽነትም፤ ቁርጠኝነትም እንደማይታይብን ነው ለኔ የሚሰማኝ። ሌላው ቀርቶ፤ ትምክህትና ጠባብነት የሚባለው ጽንፈኛ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚገለጽበት ተግባርና አመለካከት፤ የጋራ ህልውናችን

ለተመሰረተባት ሀገር ዘላቂ ዕጣ ፈንታ የማይበጅ፤ የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት ፀር በመሆኑ እንደ አንድ ህብረተሰብ አምርረን ልንታገለው ይገባል፤ ብሎ መናገር የተወሰኑ ወገኖችን ለመጉዳት ያለመ ፕሮፓጋንዳ መስሎ የሚታይበት ደረጃ ላይ መደረሱን መረዳት አያዳግትም።

እናም ከዚህ አኳያ የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶችም ጭምር ሁለቱ ተቃራኒ የአመለካከት ፅንፎች የሚገለፁበትን አክራሪ አስተሳሰብ፤ አምርሮ የመታገል አስፈላጊነት ለመላው የሀገራችን ህዝቦች ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣ ፈንታ መቃናት ሲባል በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት የሚገባው፤ የሀገራዊ ህልውና ጥያቄ እንጂ፤ ፈፅሞ አንድን የብሔር ወይም የብሔረሰብ ህዝብ፤ እንደህዝብ ኢላማ የሚያደርግ አይደለም የሚል የጋራ አቋም ላይ እንደደረሱ በተደጋጋሚ ሲገልጹ የሚሰሙበት አጋጣሚ ብዙ ቢሆንም ይህንኑ አቋማቸውን ወደ ህዝቦቻቸው አውርደው ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ግን ቁርጠኛነቱ ያላቸው አይመስሉም። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋር ፓርቲዎች፤ ይህን አሳሳቢ የአመለካከት ችግር በመታገል ረገድ ምንም ዓይነት ብዥታ መኖር የለበትም፤ የሚል የጋራ አቋማቸውን በማያሻማ መልኩ ግልጽ አድርገው ወደትግል ባለመግባታቸው የተነሳም ጉዳዩን ከብሄር ማንነት ጋር አያይዘው በማቅረብ፤ ለየራሳቸው ድብቅ አጀንዳ ማሳኪያነት ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ የሚስተዋሉት የቀለም አብዮት ናፋቂዎቹ ተቃዋሚ ቡድኖች፤ በተለይም ወጣቱን ትውልድ እያሳሳቱበት ይገኛሉ።

ይህ ዓይነቱ ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች በተጠና መልኩ የሚያቀነባብሩትና ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል በፌደራል ስርዓቱ ላይ የማሳመጽ ዓላማ ያለው የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብን አጉልቶ የሚያንፀባርቅ አክራሪ አቋም የማዛመት ስትራቴጂ፤ እያሳደረ ስላለው አሉታዊ ተጽእኖና ተጽእኖውን መቀነስ ስለሚቻልበት አማራጭ የመፍትሔ አቅጣጫ፤ በግምባር ቀደምትነት መክረው ዘክረው የማያሻማ የጋራ መግባባት ላይ መድረስና ወደ ተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት የሚጠበቅባቸው፤ በተለይም ይህቺን ሀገር ይመሩ ዘንድ በየክልሎቻቸው ህዝብ የተመረጡት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና እንዲሁም ደግሞ አጋሮቻቸው እንደሆኑ አያጠያይቅም። ይሁን እንጂ አሁን የሚስተዋለው ተጨባጭ እውነታ ያን በማድረግ በኩል ሰፊ ክፍተት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው ማለት ይቻላል። ወጣም ወረደ ግን፤ የሽብርተኝነት አደጋ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው የአንድ ጽንፍ ፖለቲካዊ፤ አልያም ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ይዘት ባለው የመብትና የዕኩልነት ጥያቄ ሽፋን የሚቀነቀን አክራሪ አስተሳሰብ፤ ከኛ አገር አጠቃላይ ሁኔታ አኳያ ስለሚገለፅበት አግባብ፤ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅድሚያ በማያሻማ ሁኔታ አንድ ዓይነት የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚጠበቅባቸው ይሰማኛል።

ይልቁንም አሁን ሀገሪቷን በመምራት ላይ የሚገኙት አራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና እንዲሁም ደግሞ የግንባሩ አጋር ፓርቲዎች፤ ለመላው የሰው ዘር አሳሳቢ የደህንነት ስጋት ምንጭ የሆነውን የሽብርተኝነት ተግባር ለማስፋፋት ለሚንቀሳቀሱት ቡድኖች መበራከት የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስድ ድፍን የዓለም ማህበረሰብ የተናገረለትን የአስተሳሰብ ጽንፈኝነት አምርሮ ስለመታገል አስፈላጊነት ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ የተሻለ የፖለቲካ ቁርጠኝነትን በሚጠይቅ የጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ አቋም መያዝ ይጠበቅባቸዋል። በአጠቃላይ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተስተዋሉ ያሉት አብዛኛዎቹ የሀገሪቷ ችግሮች፤ በዋነኛነት ከትምክህትና ከጠባብ ብሔርተኛ አመለካከት የሚመነጭ የአስተሳሰብ ፅንፈኝነት የሚገለፅባቸው ተደርገው ቢወሰዱ ተገቢነት ይኖረዋል።

እነዚህ ሁለቱ ተቃራኒ ባህሪ ያላቸው የአስተሳሰብ ጽንፎች፤ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትን በሚያበረታታ ተራማጁ አመለካከት የሚደፈቁበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀርም፤ የሃይማኖት አክራሪነትን የሚያባብስ አሉታዊ ተፅዕኗቸው ቀላል እንደማይሆንም ጭምር መገመት አይከብድም። ስለሆነም፤ መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘመናትን ባስቆጠረው ያለፈ ታሪካቸው በሌላው ዓለም ዘንድ የሚታወቁበት ጠቃሚ የጋራ ዕሴት ተደርጎ የሚወሰድላቸውን፤ ብዝሃነትን እንደ የኢትዮጵያዊ ማንነት መገለጫ ውበት የመቁጠር ባህል፤ ከዘመን አመጣሹ የፅንፈኝነት ወረርሽኝ መታደግ የሚችሉበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የመቀየስ ጉዳይ፤ ለነገ የማይባል እጅግ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ልናሰምርበት ይገባል። ወቅታዊው የአስተሳሰብ ቀውስ በሀገራችን ህዝቦች ዕርስ በርስ

ተከባብሮና ተፈቃቅሮ የመኖር ጠቃሚ የጋራ ባህል ላይ እያሳደረ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በመከላከል ረገድ፤ የፌደራሉ መንግስትና እንዲሁም ደግሞ የየክልሎቹ መስተዳደሮች የመሪ ተዋናይነቱን ሚና መጫወት እንደሚጠበቅባቸውም የሚያከራክር አይሆንም። በተረፈ ግን እኔ እዚህ ላይ አብቅቻለሁ። ***መዓሰላማት!***